መጋቢት 5 ቀን 2004 ዓ.ም.(13-03-2012)

# የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ

"እምብዛም ሞኝነት፣ተለያይቶ ጉዞ ለበግም አልበጃት
አስራ ሁለት ሆና አንድ ተኩላ ፈጃት"

በአንድ ወቅት ላይ በዛ ያሉ በጎች ተበታትነው ሳር የሚግጡበት መስክ ነበር፡፤በየእለቱ አንድ የተራበ ተኩላ እየተከታተለ ተራ በተራ ሳያስቡት እያሳደደ ሁሉንም እንክት አድርጎ ጨረሳቸው።ተኩላው በቁመትም ሆነ በጥንካሬ ከበጎቹ የተሻለ አልነበረም።በብዛትም ሆነ በጉልበት የበጎቹ ወገን ያመዝናል።የጎደላቸው ነገር ቢኖር ጥቃቱን ለመቋቋም ቆርጠው አለመነሳታቸው ነው።ብቻ ለብቻ እንኳን ለመቋቋም ባይችሉ እንደብዛታቸው ፣ከፊት፣ከኋላ፣ከጎንና ከጎን ከበው ፣ቀንድ ያለው በቀንዱ አለያም በግንባሩ እየቀጠቀጠ ድራሹን ያጠፉት ነበር።እንዲያም ቢያደርጉ ኖሮ ተራ በተራ ለመበላት ቀርቶ ለመነከስም ባልበቁ ነበር።በመበታተናቸውና ባለመተባበራቸው ግን ከአደጋው ሊያመልጡ አልቻሉም፤ሁሉም በቀን ልዩነት የተራበ ተኩላ ሲሳይ ሆኑ። ይህ የቀድሞ ምሳሌ  እኛ ኢትዮጵያውያን አሁን ያለንበትን ሁኔታ ይገልጸዋል ብዬ እገምታለሁ።በአገራችንና በእኛ በሕዝቦቿ ላይ የደረሰው ተደጋጋሚ ችግርና መከራ እየጨመረና እየሰፋ መሄዱን ማንኛችንም አንዘነጋውም።ችግሩ በበዛ ቁጥር መፍትሄ ይሆናል ብለን የምናስበውም መንገድና ዘዴ እንዲሁ የበዛ ነው።እነዚህ በተለያዩ ጊዜ በተለያዩ ቡድኖችም ሆነ የማህበረሰብ አባላት የሚነደፉ መፍትሄዎች ሁሉም ከችግሩ ለመላቀቅ የሚረዱ ናቸው ብሎ ሙሉ ለሙሉ መቀበል አይቻልም።በተመክሮም አንዳንዴ መፍትሄ ተብለው የቀረቡ ሃሳቦች ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው እየበዛ ችግሩን ውስብስብ እንዳደርጉት በአሳለፍነው ተመክሮ ተገንዝበናል።

ምንም እንኳን ዘላቂ መፍትሄ ባይሆኑም ለችግሩ ትኩረት ሰጥቶ መፍትሄ ይሆናል ብሎ ሃሳብ ማቅረብና መንገድ መቀየስ በብዙ መልኩ ችግሩን ተቀብሎ ከመቀመጥ የተሻለ ነው።የቀረበው ሃሳብ ደግሞ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን መመካከርና፣አንዱን  ከአንዱ ጋር አመዛዝኖ የተሻለውን ተቀብሎ መሄድ ለስኬቱ ዋስትና ከመሆኑም በላይ ሃይልን ያሰባስባል።የተሰባሰበ ሃይል ደግሞ የሚመጣበትን ጥቃት ለመቋቋም ብሎም ለማስወገድና ለመርታት መሳሪያ ነው። በሌላውም ዙሪያ መፍትሄ ተብሎ የሚቀርብ አሳብ ያለውን ችግር ሳያስወግድ እንደውም ችግሩን ለማስወገድ የሚችለውን ሃይል ለመበታተን ሆን ተብሎ ከጠላት ጎራ የሚቀመም የጥፋት መርዝ ሊሆን እንደሚችል ተገንዝቦ ከብዙ አቅጣጫ መፈተንና መፈተሽ ይኖርበታል። "እናቴን ያገባ ሁሉ አባቴ ነው"ወይም "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" የሚል አስተሳሰብ ይዞ ሁሉንም በማቀፍና በማመን መጓዝ አደገኛ ነው።እዚህ ላይ ሁሉንም መጠራጠርና መራቅ ያስፈልጋል ለማለት ሳይሆን "ያልጠረጠረ ተመነጠረ" የሚለውንም በተግባር የተፈተነ ልምድ መዘንጋት እንደሌለበት ለማስታወስ ነው።ለመተማመን መቀራረብ፣መፈታተሽና መነጋገር አንዱና  ዋናው ቁልፍ ነው።በዚህ ደረጃውን በጠበቀ ሂደት ላይ የተገነባ መተማመን ደግሞ ወደ ማይፈርስና ወደማይናጋ
አንድነት ያመራል።ያ ጠንካራ አንድነት ደግሞ ወደ ዘላቂ ድል ይወስዳል።በተናጠል ተበታትኖ፣ወይም በተወሰነ ሃይል ብቻ ተማምኖ የሚደረገው ትግል ከድሉ ይበልጥ ውድቀቱና ሽንፈቱ ያመዝናል።ሁሉንም የሚያረካ ለውጥ አያመጣም።ትርፉ ጉዳት ነው፤አስራ ሁለት ሆነው በአንድ ተኩላ እንደተበሉት የበግ ቤተሰብ መሆን ነው።
እንደ አጋጣሚ እንኳን ቢሳካ የሚገኘው የትግል ውጤት ውሎ አያድርም፤ዕድሜው አጭር ይሆናል።በውስጡ ይዞት የሚመጣው ችግርና ድክመቶች ስላሉት ለዳግመኛ ችግርና ትግል ይዳርጋል። የጉዳዩ ባለቤቶች የሆኑትን ሁሉንም ስላላሳተፈ በቅራኔ የተተበተበ፣የብዙሃኑ ተቀባይነት የማይኖረው፣ የጥቂቶችን ፍላጎት የሚያንጸባርቅና የሚያስተናግድ ይሆናል። በዚህ

መልክ የሚፈጠረው ስብስብ የሚያካሂደው ትግል ውጤቱ ችግሩ ሳይወገድ የችግሩ ባለቤቶችና ፈጣሪዎች በሌላ ስምና በተለዬ መልክ እየተቀያየሩ የሚቀጥሉበትን ዕድል መፍጠር ይሆናል።

**የኢትዮጵያን ሕዝብ ያላሳተፈ፣የኢትዮጵያን አገራዊ አንድነት ያላማከለ፤**

**የዲሞክራሲን ስርዓት ያላሰፈነ፣ፍትህና ሰብአዊ መብትን ያላስከበረ ስርዓት**

**በአሸዋ ላይ እንደተሠራ ቤት በቀላል ንፋስ የሚደረመስ መሆኑን ከኛና ከሌሎች ታሪኮች አይተናል።አሁንም እየተገነዘብን ነው።**

**ለወደፊቱም በዚያ አይነት የነጠላ ትግል የሚገኝ ጊዜያዊ ድል በተቃውሞ ነውጥ ለመሰባበር የሚበቁበትን ዕድልና በር ከመክፈት የተሻለ ለውጥ አያመጣም።**

በተለይም ለአገሪቱ ሕዝብ ሳይሆን ለውጭ ሃይሎች ቅድሚያና የወሳኝነትን መብት የሚሰጥ፣በነሱ ቡራኬ፣ ምክርና እርዳታ የሚተማመን፣ እነሱን ተገን ያደረገና በነሱ ፍላጎት የሚሽከረከር ሃይል መፍትሔ አያመጣም።የባርነት ሰንሰለት እንዳይበጠስ የሚረዳ፣ እንደ ኢሕአዴግ ባንዳ ሆኖ የሚያገለግል ወዶ ገባ የነጻነት ጠላት ነው።
በዚህ መልክ የሚንቀሳቀስ ድርጅትም ሆነ ቡድን በሥልጣን ላይ ካለው ከኢሕአዴግ ቡድን የተለዬ  ሳይሆን እሱን ተክቶ ስርዓቱን ተሸክሞ ለመሄድ የተዘጋጀ ተለዋጭ ጎማ ወይም በፎቶ ኮፒ ለመሥራት የሚሻ ነው።ፍላጎቱ ሥልጣን እንጂ የአገር ልዕልና፣ የሕዝቦች እኩልነት አይደለም።የለውጥና የዴሞክራሲ ታርጋ ለጥፎ በውስጡ ሰባሪ ሃይሎችን አሳፍሮ ወደ ገደል የሚጓዝ ባቡር አይነት ነው።በተቃውሞ ጎራ የተሰለፉት ከዚህ አይነቱ ምግባርና ግንኙነት የራቁ እንደሆኑ ባልጠራጠርም ከእኔ ምስክርነት ይበልጥ የሚያራምዱት አቋም ማንነታቸውን ይገልጻል።
ምናልባትም በኢትዮጵያውያኑ የትግል ጉዞ  ውስጥ በአሳሳች አቅጣጫ የሚጓዝ ባቡር ቢኖር በሕዝብ ግፊት በትክክለኛው ሃዲድ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ እንዲጓዝ፣እምቢም ካለ ከሃዲዱ እንዲወጣና በሃዲዱ ላይ የኢትዮጵያዊነት ታርጋ ለጥፎ፣አገራዊ ጥቅምን ለማስከበር፣ሕዝቦችን አሳፍሮ የሚጓዝ ባቡር እንዲሽከረከር ማድረግ አስፈላጊና ተገቢ ነው።

በዚህ ሕዝባዊ ባቡር ውስጥ ሊሳፈሩ የሚችሉ ብዙ የተበታተኑ ሃይሎች አሉ። ከመበታተናቸው የተነሳ ሃይል የላቸውም፤ ደካሞች ናቸው።እንኳንስ ኢሕአዴግን የመሰለ የጦር መሣሪያ፣የወታደር፣የገንዘብ፣አቅም ያለውን፣ በዓለም አቀፍ ዘራፊ መንግሥታትና ድርጅቶች የሚረዳ ጸረ ኢትዮጵያ ሃይል ቀርቶ ጥቃቅን ውስጣዊ ችግሮችን እንኳን ለማስወገድ ብቃት የላቸውም፤በየእለቱ እየተፈረካከሱ እርስ በርሳቸው እየተባሉ መሳቂያ መሳለቂያ ሆነዋል።የሚመሳሰል እምነትና ፍላጎት ካላቸው ጋር አብሮ ለመሥራት ፍላጎት የላቸውም።አንዱ አብረን እንሥራ!እንተባበር ብሎ ሲጠይቅ ጥሪውን በቀና ዓይን ተመልክቶ መልስ ከመስጠትና ለመተባበር ፈቃደኛ ከመሆን ይልቅ በጥሪው ላይ ጥሪ እያቀረቡ፣ከማን አንሼ ውድድር ውስጥ መግባትና መጠላለፍን  ዋና ሥራ አድርገው ይዘውታል።ተወናብደው ሕዝብን በማወናበድ ጊዜና ጉልበታቸውን ሲከሰክሱ ይታያሉ።ቀድሞ ለቀረበ ጥሪ መልስ ሳይሰጡና እንዳልሰማ በመሆን አዲስ ተመሳሳይ ጥሪ ያቀርባሉ።የድርጅቶችንና የጥሪውን ብዛት ሲመለከቱት ለመሆኑ ስንት ኢትዮጵያ ነች ያለችው? ያሰኛል።
ሁሉም የሚናገረው፣የሚጽፈው አንድ አይነት ነው።ለመተባበር ግን እንቅፋት የሆነበት የዓላማ ልዩነት ሳይሆን አጉል ጥርጣሬ፣አለመተማመን፣የራስን የሥልጣን ፍላጎት ከአገራዊ ጥቅም

በላይ በማየትና በመንከባከብ፣ከሌላው ጋር ብተባበርና ብሠራ፣በብዙሃኑ ፍላጎትና አመራር ውስጥ ብካተት፣ያለኝ የበላይነት ቦታ ይነካብኛል ወይም ሥልጣን አጣለሁ ከሚለው ስጋትና እራስ ወዳድነት የመነጨ ድክመት ከመሆን የተለየ ምክንያት አይኖረውም።
በዋና ዋና ነጥቦችና ዓላማዎች ላይ ከተስማሙ በሌሎቹ ጥቃቅን የግልና የቡድን ፍላጎት ላይ ማተኮርና ከአገራዊ ጥሪ በላይ ክብደት መስጠት ከስህተትም በላይ ብሔራዊ ክህደት ነው። እያንዳንዱ ድርጅት በተናጠል የትም ሊደርስ እንደማይችል መገንዘብ አለበት። የቆመው ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም ከሆነ የራሱን ሥልጣን፣ዝናና ጥቅም ብቻ ሳይሆን ህይወቱንም ቢያጣ ቅር ሊለው አይገባም። የቆመው ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም ከሆነ ከሌሎቹ መሰል ድርጅቶች፣ቡድኖችና ግለሰቦች ያገሪቱ ጉዳይ ያገባናል ከሚሉ ዜጎች ጋር ተገናኝቶ መምከርና በአንድ የጋራ አመራር ሥር ትግልን ለማቀናጀት የበኩሉን ድርሻ ማበርከት ይጠበቅበታል።
ለግንባር ምሥረታው የሚያደርጉት አስተዋጽኦና ጥረት ፣አብሮ ለመሥራት ፍላጎት ማሳየት ደግሞ ማንነታቸው የሚታወቅበትና የሚመዘኑበት መለኪያ ይሆናል። እያንዳንዱ በተቃዋሚ ጎራ የተሰለፈ ሃቀኛ ታጋይና ለውጥ ፈላጊ ዜጋ ለጋራ ግንባር ምሥረታ የድርሻውን ማበርከት ይኖርበታል።ለአንድ ድርጅት ወይም ቡድን የሚሰጠውን ድጋፍና እርዳታ ለትልቁና አስተማማኝ ለሆነው አገር አቀፍ የአንድነት ግንባር ቢያውለው የሚያበረክተው የገንዘብ፣የእውቀትና የጉልበት አስተዋጽኦ ከንቱ አይሆንም። የሃይል ሚዛንን ያገናዘበ፣ዓላማን በግልጽ ያስቀመጠ የጋራ ግንባር ሳይመሰረትና የጋራ ግንባሩ ተስማምቶ በሚያወጣውና በሚቀይሰው የትግል ስልት ካልተሳተፉ ውጤቱ እንደ በጓ ተበታትኖ እየጮሁ ለበላተኛው ቀበሮ ተመችቶ መገኘትና ማለቅ ይሆናል።

በአለፈው ጊዜ እንደታዘብኩት ከዘጠኝ የማያንሱ ስብስቦች ኑ.... ተከተሉን የሚል ጥሪ አስተላልፈዋል።ከነዚህም ውስጥ ከ18 ወራት በፊት ሁሉን አቀፍ የአንድነት ግንባር ምሥረታ ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ፣ከዚያ በኋላ የግንቦት ሰባት፣ቀጥሎም የበቃ፣የክተት፣የእስከመቼ፣የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ፣የኢሕአፓና ጥምረት አሁን ደግሞ በቅርቡ የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ካውንስል በሚል ስም የአንድነት ግንባር ጥሪ አስተላልፈዋል።
ለመሆኑ አንዱ ሲጠራ ሌላው ምን መልስ ሰጠ?ተደጋጋሚ ጥሪ ለምን አስፈለገ?የዓላማ ልዩነት በመኖሩ ነው?አብሮ ለመሥራትና አንድ ግንባር ለመፍጠር ምን አገዳቸው? አሁንስ አንዱ ከሌላው ጋር አብሮ ለመሥራትና ጠንካራ ግንባር ለመፍጠር ፍላጎት አላቸው ወይ? ግንባር ከመመስረትና ስም ከማውጣታቸው በፊት ሕዝባዊ ስብሰባ ጠርተው ድጋፍና ሃሳብ ሰብስበዋል? ወይስ እነሱ ባወጡትና በሚፈልጉት መንገድ ተደራጅተው ሕዝብ አድራጊ ፈጣሪና ወሳኝ ሳይሆን አጃቢ እንዲሆናቸው ነው የሚፈልጉት? ላቀረቡት ጥሪ ምን መልስ አገኙ? አሁንስ የሚገኙበት ሁኔታ ምን ይመስላል? ለበለጠ መግባባትና ግንዛቤ እስከአሁን ጥሪ ያደረጉት ስብስቦች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ መስጠት አለባቸው ብዬ እገምታለሁ።ሕዝቡም ሊጠይቃቸው ይገባል።

ለማጠቃለል ያህል፣ለማሳሰብ የምወደው በየቦታው ተበታትናችሁ በልዩ ልዩ ስም የምትንቀሳቀሱ ድርጅቶች፣ቡድኖችና ግለሰቦች ያላችሁበትንና ያለባችሁን ድክመት መርምራችሁ ወደተሻለ ውጤት ሊያመራችሁ የሚችለውን፣ ሁላችሁንም ያሳተፈና ያስተባበረ፣ የወገናችንና የአገራችንን አንድነትና ነጻነት በሚያረጋግጠው የትግል ጎዳና ትገቡ ዘንዴ የአንድነት ግንባር ለመመሥረት የሚደረገውን ጥረትና ሁሉን አቀፍ የአንድነት ግንባር ምሥረታ ያደረገዉን የጉባኤ ጥሪ የእሱ ወይም የነእሱ ሳይሆን የእኛ ብላችሁ በመቀበል እንድትተባበሩ ነው።በየፊናችሁ የምታደርጉትም ጥሪ ክፍፍልን እንጂ አንድነትን አያመጣም።የምትሉትን ከምትሠሩት ጋር ማመሳከር ይኖርባችኋል። የአገር ጥቅም ከድርጅቶች ጥቅም በታች ታይቶ በዝምታ፣በፍርሃትና በይሉኝታ ሊታለፍ አይገባውም።በዚህ ዙሪያ የተለያዩት የብዙሃን የዜና አውታሮች፣የቴሌቪዥንና፣የራዲዮ ጣቢያዎች፣ድህረ ገጾችና የነጻ ጋዜጦች በድፍረት መጠየቅ አለባቸው።በዚህ ሙያና መስክ የተሰማሩት ለሥራ ዕድል ወይም ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት የአንድ ድርጅት አፍና ጆሮ ሆነው ከማገልገል፣ የማይፈልጉትን አስተያየት እያፈኑ ለሕዝብ ጆሮ እንዳይደርስ የሳንሱር ጫና ከማስቀመጥና

እውነቱ ተደብቆ እንዲቀር ከማድረግ ይልቅ፣ በነጻ ለነጻ ሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ በዚህ አጋጣሚ ላሳስባቸው እወዳለሁ።አለያማ  እራሱ ነጻነት የማያውቅ፣የድርጅቶች አፈ ቀላጤ የሆነ ጋዜጠኛ ለነጻ የህዝብ ድምጽ ሊቆምና ሊከራከር የሞራል ብቃት አይኖረውም።

ያልተደራጀው ግን የአገሩ ጉዳይ እንቅልፍ ነስቶት እያሳሰበው የሚኖረው ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች በተናጠል  የሚያደርጉት ጉዞና ጥሪ የትም እንደማያደርስና ውጤት አልባ እንደሆነ ሊያስገነዝባቸውና ወደ አንድነት ግንባሩ ምሥረታ ፊታቸውን እንዲያዞሩ ማስገደድ ይኖርበታል።በችኮላና በቃላት ተወናብዶ ለማያዋጣ ትግል መሣሪያና መከታ መሆን፣ገንዘቡን፣እውቀቱን፣ጊዜውንና ጉልበቱን ማፍሰስ አይኖርበትም።ካለፈው መማር አለበት።ተስፋ ቆርጦም እየተበሳጩ ከዳር መቆምና መታዘብ አማራጭ አይሆንም።ግልጽ ዓላማ ነድፎ፣የትግሉን ቅደም ተከተል አጥንቶና አጢኖ፣ የሃይል አሰላለፍን ገምግሞ፣ወዳጅና ጠላትን ለይቶ በሚሄድ በሚያስተማምነው ድርጅታዊ ዝግጅትና አሠራር በተሰለፈ ጎራ ውስጥ መሳተፍ ወይም መርዳት የትውልድን አደራና ድርሻ መወጣት ነው።በችኮላና በስሜት ብቻ ተገዝቶ የሚሰሩት ነገር “የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ” ወይም “ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል” የሚለውን የአበው አባባል በተግባር መግለጽ ስለሆነ በሰከነ አይምሮ ማሰብ ማውጣትና ማውረድ ግድ ይላል።ሥራው የችኮላ ወይም የሆያሆዬ ጨዋታ ሳይሆን የአገርን ህልውና የወደፊቱን ትውልድ ዕድል የሚወስን አላፊነትንና አስተዋይነትን የሚጠይቅ ግዙፍ አደራ ነው። ስለሆነም በሰከነ አይምሮ የተሠራ ሥራ ከስህተት የኋላኋላም ከጸጸት ያድናል። የእስከዛሬው ስህተት መከሰት የዚህ አይነት አካሄድ አለመኖር ውጤት ነው።በጋራ መክሮና ዘክሮ ፣የጋራ ግንባር ፈጥሮ ያለመታገል ያመጣው ውድቀት ነው።በሕዝቡ ውስጥ ሆነው ሳይታገሉና ሳያታግሉ የውጭ ሃይልን ተማምኖ በሕዝብ ትከሻ ላይ የሚሹትን ለመጫን መሞከር ተቀባይነት አይኖረውም።

ለሚያስተማምን ድል የሚያስተማምን አገር አቀፍ ግንባር ወሳኝና መሰረት ነው። ይህም ግንባር እውጭ ባሉት ሃይሎች ብቻ ሳይሆን በአገር ውስጥ ካሉት ጋር መያያዝ ይኖርበታል።እርግጥ በአገር ውስጥ ያሉት ለመንቀሳቀስ ያላቸው ዕድል የመነመነ መሆኑ ባይካድም በሚገኘው ዕድል አብሮ መሥራትና ትግሉን ማያያዝ በጣም አስፈላጊና ወሳኝ ነው።የውጬ ሃይል ለመንቀሳቀስ ባለው ዕድል፣በገንዘብና በማተሪያል ትልቅ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል።ከዚያ በተረፈ ግን ወሳኝና ባለቤት ሊሆን አይችልም።ወሳኝና ባለቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።

ከትግል በፊት አንድነት ይቅደም!
አገር ሳይኖር ሥልጣን አይኖርም!!

ከተስፋሚካኤል በላቸው ተክሊዬን።